# የአሲምባ ውይይት መድረክ ፕሮግራም

ቅዳሜ ሰኔ ፩ ቀን ፪፻፺፰

(Saturday June 8, 2005)

በዚህ ዕለት የአሲምባ ውይይት መድረክ **ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳን** በክብር እንግድነት በመጋበዝ ስለሀገራችን ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁናቴና በቅርቡ ለኦሮሞ ዴሞክራሲ ግንባር አመራር አባል ዶ/ር በያና ሱባ የላኩትን ግልጽ ደብዳቤ አስመልክቶና ስለ ኦሮሞ ሕዝብ የማያጠራጥር ኢትዮጵያዊነት ታሪክ ያወያዩናል።

የአሲምባ ውይይት መድረክ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ስለሀገራችን ኢትዮጵያ የሚወያዩበትና በሳል ሃሳቦች የሚንሸራሸሩበት ዴሞክራሲያዊ ነጻ የውይይት መድረክ ነው።

መድረኩ ዘወትር ቅዳሜ እንደ ዋሺንግተን ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ ሁለት ሰዓት (2:00 PM) ጀምሮ ይከፈታል።

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል!

ከዚህ ማስታወቂያ ጋር አባሪ ጽሁፎች ሳላሉ ወረድ ብለው ያንብቧቸው:-

1. የዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳን ግልጽ ደብዳቤ
2. የዶ/ር በያና መልስ በአማርኛ ተተርጉሞ
3. በእንግሊዝኛ ለግልጹ ደብዳቤ የተሰጠ አስተያየት
4. ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ ዶ/ር በያና ለጻፉት መልስ የሰጡት ምላሽ

## ከ ዶ/ር ፍቅሬ ቶለሳ ጂግሳ

## ግልጽ ደብዳቤ ለ ዶ/ር በያና ሱባ

ይድረስ ለተክበሩ ዶ/ር በያና ሱባ፣ የኦሮሞ ዲሞክራሲ ግንባር አመራር አባል በአሉበት፡፡

ይህን ደብዳቤ እንድ ጽፍልዎት ያነሳሱኝ ምክንያቶች ርስዎ በቅርቡ ለኢሳት ሬዲዮ የሰጡት ቃለመጠይቅ እና አሁን ርስዎ የሚመሩት ከሳምንታት በፊት የተቋቋመው "የ ኦሮሞ ዲሞክራቲክ ግንባር" የወሰዳቸው አቋሞች ናቸው፡፡ የርስዎ ቃለመጠይቅና የግንባሩ አዲስ አቋሞች በግሌ እንደ አስደሰቱኝ በዚህ አጋጣሚ ልገልጽልዎ እወዳለሁ፡፡

ለኔ እንደሚገባኝ፣ አዲሱ ግንባራችሁ የኦሮሞን ህዝብ እና የእናንተንም ኢትዮጵያዊነት ያለማወላወል አምኖ፣ የኦሮሞ ሕዝብ ሃገርም "ኦሮምያ" የተባለችው ጠባብ ምድር ብቻ ሳትሆን መላዋ ኢትዮጵያ መሆኑን ተቀብሎ፣ የኦሮሞን ህዝብ ዕጣ ፈንታ ከ መላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር አጣምሮ ለመታገል አብስሯል፡፡ ይህም አቋም ለኦሮሞ ህዝብ ታላቅ የፖለቲካ እመርታ ነው፡፡ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ከጥንቱ፣ ከጠዋቱ፣ ከጥንስሱ ይህን ጥርት ያለ አቋም ይዞ ቢሆን ኖር ምናልባት ዛሬ ኢትዮጵያን የሚመራት እሱ በሆነ ነበር፡፡ የመላውን የኢትዮጵያ ህዝቦች ድጋፍና ትብብር ያገኝ ነበርና፡፡ ከዚህም በላይ ያ ሁሉ ደም ላይፈስ፣ ያ ሁሉ ሰው ላይፈናቀል፣ ላይሰደድና ለእስር ላይዳረግ በቻለ ነበር፡፡

ርግጥ ለ ኦሮሞ ዝርያዎች በግለሰብ ደረጃም ሆነ አልሆነ ኢትዮጵያን መምራትና ማስተዳድር አዲስ ክስተት አይደለም፡፡ ከዛሬ 3500 ዓመታት ጀምሮ ይህን ሲያደርጉ ኖረዋል፡፡ ከ ዛሬ ሁለት ሺ ዓመታት በፊት በአመራር ላይ ከነበሩ ኦሮሞዎች መሃል እንዷት ሴት እና ወንድ ለመጥቀስ ያህል በመርዌ የነገሠችው የሕንደኬዋ ንግሥት፣ የመደባይዋ ጎሳ ሚያኖን በአፄ ፈንታሌ ጊዜ ከፍተኛ ሥልጣን የነበራትና የጂማውን ንጉሥ መጋልን እንዘክራለን፡፡ ይህም የጂማ ትልቅ ንጉሥ፣ የመደባይን ካህናት ይዞ፣ በአፋር መርከብ ተሳፍሮ ፖርቱጋልን እና ሥፔንን ለ አጭር ጊዜ ከመያዙም በላይ እየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ከአስራ አንድ የኢትዮጵ ዝርያዎች ነገሥታት ወ ጠቢባን ወንድሞቹ ጋር ሆኖ፣ ኢትዮጵያ ግዛት ላይ የታየችውን ኮከብ ተከትሎ ወደ ቤተልሄም ተጊዞ ለዓለሙ ሁሉ ፈጣሪ ለእየሱስ ክርቶስ ጋዳ እንዳበረከተ ታሪክ ዘግቧል፡፡

ባለፈው 3500 ዓመታት፣ መጀመሪያ በአባታቸው በኢትዮጵ ስርወመንግሥት ስር፣ በኋላም በሰለሞናውያን እና ዛጉዌ ስርወመንግሥት ውስጥ አማራው ያላደረገውን በንጉሥነት፣ በንግሥትነት፣ በንጉሠነገሥትነት እና በንግሥተነገሥታትነት፣ እንዲሁም በባለሙሉሥልጣን እንደራሴነት እና በራስነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያን ገዝተዋል፡፡ አስተድድረዋል፡፡ ለአብነት ያህል፣ ከቅርቦቹ፣ ማለትም ባለፉት 800 ዓመታት ብቻ ዕላይ በተጠቀሱት ማዕረጎች ኢትዮጵያን የመሩ ጥቂት የኦሮሞ ዝርያዎችን እንድጠቅስ ይፍቀዱልኝና የሚከተሉትን ስሞች ላስፍር፡፡ --

የሰለሞንን ስርወመንግስት በሸዋ ያስመለሰው የኦሮሞዋ የጊፍቲ መንዲያ ልጅ ንጉሠነገሥት ይኩኖአምላክ፣ እሱም በበኩሉ ኦሮሞዋን ጃን ሞገሳ ዳዲን አግብቶ እሷን የኢትዮጵያ ንግሥተነሥታት አድርጓት፣ የሷ የልጅልጅ አፄ በዕደማርያም ነግሶ የደዋሮውን ኦሮሞ ሙስሊም የገራድ ሞሃመድ በንቲን ልጅ ክርስትና አንስቶ፣ ስሟን "ጃን ክብራ እሌኒ ዳግማዊት" ብሎ ያነገሣት፣ ከዛም በኋላ የሱ እና የሷ ልጅ አፄ ናኦድ አግብቶአት "ናኦደ ሞገሳ እሌኒ ሳልሳዊ" ብሎ ያነገሣት የሃረሩ ሙስሊም ኦሮሞ የቱሉ በዴሳ ልጅ፣ የሱ ልጅ አፄ ልብነድንግል ሕፃን ልጅ ሳለ ደግሞ ኦሮሞዎቹ እናቱ፣ የሴትና የወንድ ኦሮሞ አያቶቹ

እሌኒ ናኦድ ሞገሳ፣ ጃን ክብራ እሌኒ ዳግማዊት እና ቱሉ በዴሳ ሆነው በብስለት፣ በህብረትና በፍቅር መላዋን ኢትይዮጵያን እየመሩ በብቁነት አስተዳድረዋል፡፡ የንግሥት እሌኒ ሞገሳ ወንድም ዶሪ ቱሉ በዴሳ ዘውድ ደፍቶ፣ ባህር-ነጋሽ ተብሎ በቀይ ባህር፣ በትግራይና በአርትራ ነግሦ ነበር፡፡ እሱ ከሞተ በኋላ ደግሞ የእሱ ልጅ ባህር-ነጋሽ ይስሃቅ ዶሪ በሱ ቦታ ነግሦ የእሱን ግዛቶች በሚገባ አስተዳድሯል፡፡ በዚህ አይነት አያሌ ኦሮሞዎች እስከ ፍጻሜ መንግሥት፣ ማለትም የሰለሞን ሥርወመንግሥት ተዳክሞ በዘመነ-መሳፍንት እስከሚተካ ድረስ ኦሮሞዎች ኢትይጵያን ቀጥ አድርገው ገዝተዋል፡፡ ዘመነ-መሳፍንት የተጀመረውም የሊበን ጎሳ በሆነችው በወሎዋ ኦሮሞ ንግሥት ዋቢ ልጅ በ አፄ ኢዮአስ አገዛዝ ጊዜ ነበር፡፡ የሱ እንደራሴ የትግሬው ሥሁል ሚካኤል ተጣሉትና በሻሽ አንቀው ገደሉት፡፡ ከዛ ራሳቸው መንገሥ ስለፈሩ፣ የነገሥታት ልጆች እስኪነግሱ ድረስ ከሚታሰሩበት ከወህኒ-አምባ ዮሃንስ የተባሉ፣ የ 71 ዓመት ድኩም (እጀ-ቆራጣ) ለይስሙላ "በሰለሞን" ዙፋን ላይ አስቀምጠው (አጋድመው ማለት ይሻላል) እሳቸው ንጉስ ሺሚ-ሻሪ ሆነው፣ ከእኘህም ተጣልተው፣ እኚህንም ገለው፣ ሕጻን ልጅ ሾመው እሳቸው በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያን አንቀጥቅጠው ገዟት፡፡ ከሳቸው በኋላ ደግሞ የወሎ ኦሮሞዎች ከትልቁ እስከ ትንሹ ራስ አሊ ድረስ እንዲሁ የይስሙላ ንጉሥ አልጋው ላይ እያስተኙ፣ እስከ አፄ ቴዎድሮስ መነሳት ድረስ ገዙ፡፡ ታዲያ ኦሮሞዎች እንደዚህ አድርገው ኢትዮጵያን ሲገዙ አማራዎች ፈንጠር ብለው ቆመው የነሱን መንግሥትና የኢትዮጵያን ዳር ድንበር በጀግንነት ይጠብቁ ነበር እንጂ ወደዙፋኑ አካባቢ ዝርም አላሉ፡፡ በዚህ አይነት፣ አፄ ቴዎድሮስ አማራ ከተባሉ፣ ካፄ ቴዎድሮስ በቀር አንድም አማራ አልነገሠም ማለት ነው፡፡ አፄ ቴዎድሮስም ቢሆኑ (እዚህ ላይ፣ እሳቸው አማራ ናቸው ብለው የሚኮሩትን ጎንደሬዎች ይቅርታ እየጠየቅሁ) ትልቁ ባለታሪክ አለቃ አጽመጊዮርጊስ የጋላ ታሪክ በሚለው መጽሃፋቸው እንደሚተርኩልን አፄ ቴዎድሮስ አማራ አልነበሩም፡፡ ቋሬ (የቋራ ሰው) ነበሩ እንጂ፡፡ እንደ እሳቸው አባባል፣ ቋሬዎች የራሳቸው ቋንቋ የነበራቸው አማራ ያልሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡ አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውም ቢሁኑ በየማህተማቸው ላይ ፣ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፣ ንጉሠነገሥት ዘኢትዮጵያ) ብለው የአጋዚና የይሁዳ ዘር መሆናቸውን ነበር እያረጋገጡ የሚያውጁት፡፡ በአባታቸው በልጅ ኃይሉ በኩል ቛሬ ቢሆኑም በእርግጥም በእናታቸው በኩል ሰለሞናዊ የነገሥታት ዝርያ ነበሩና፡፡ እሳቸው የጠሩ አማራ ነበሩ ከተባለም እንኩዋን፣ "ንጉሠነግሥት ቴዎድሮስ ዘእምነገደ አምሃራ" ብለው ያላወጁት ከፖለቲካው በተጨማሪ የ አማራ ሥርወመንግሥት ስለአልነበረ ነው፡፡ ይህም የሚጠቁመው አማራ የራሱ ሥርወመንግሥት ኖሮት ኢትይጵያን ገዝቶ እንደማያውቅ ነው፡፡ እስከነአካቴው እሳቸው ይሉት የነበረው "በጋሎች ተይዞ የነበረውን የአባቶቼን የእስራኣላውያንን መንግሥት እግዚአብሄር መለሰልኝ፣ " ነበር፡፡ እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት እሳቸው "ጋሎች" ሲሉ መሳደባቸው ሳይሆን በዛን ጊዜ አነጋገር "ኦሮሞ" ለማለት ፈልገው ነው፡፡ እጅግ የሚያፈቅሯት ሚስታቸው እቴጌ ተዋበች "ጋላ" ነበሩና የሚስታቸውን ወላጆች አይሰድቡም፡፡ ከአፋቸው የፈለቀው ሃቅ ግን ከሳቸው በፊት ኦሮሞዎች ኢትዮጵያን መግዛታቸው ነው፡፡ ታዲያ በኛ ዘመን፣ ኢትዮጵያን በስርወመንግሥት የገዛው አማራ ነው የሚለው ነጭ ውሸት ከየት መጣ? መልሱ ግልጥና ሁለት ነው፡፡-- አንድኛው አማራውን መስፈራርቾ (ፈረንጆቹ እንደሚሉት "ቡጊማን") አድርገው ሥልጣን ለመያዝ ከሚፈልጉ ፖለቲከኞች ብብትና አፍ ይህ ቅጥፈት የወጣ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ፣ የሃገራቸውን ታሪክ ጠንቅቀው ከማያውቁ ጥራዝነጠቅ ግለሰቦች አንደበት የፈለቀ ነው፡፡ ምስኪን አማሮች! ቋንቋቸው ተወዶ የመንግሥት ቋንቋ በመሆኑ እነሱ ገዥዎች መስለው ታዩ፡፡ እነሱ በርግጥ ኢትዮጵያን ገዝተው ቢሆንማ ኖሮ የአማራው ህዝብ ኑሮ ከሌሎቹ እትዮጵያውያን እጅግ የተለየና የተሻለ በሆነ ነበር፡፡ የሚያሳዝነው ነገር፣ ባልዋሉበት ዋሉ፣ ተብለው ተሰቃዩ፡፡ የሆነ ሆኖ፣ በቅርቡና በእኛ ዘመን የነበሩትና የአሉት ኢትዮጵያን የመሩት የኦሮሞ ዝርያዎች ቁጥር እንኳ በዚህ ፅሁፍ ተዘርዝሮ ስለማያልቅ አልፈዋለሁ፡፡ የነሱን ዝርዝር ማየት ከሹ የዛሬ 17 ዓመት አካባቢ ኢትዮጵያን ሪቪው መፅሔት ላይ ያወጣሁትን "ኖብልስ ኦፍ ኦሮሞ ዲሰንት ሁ ሩልድ ኢትዮጵያ" የተሰኘውን የምርምር ሥራዬን ያጢኑት፡፡

*ክቡር ዶ/ር በያና ሱባ፣ ወደ ዐቢዩ ጉዳይ ልመለስና፣ አሁን የወሰናችሁት ውሳኔ መልካም ሲሆን፣ አንድ የማይቀር ዋና ነገር አለ፡፡ እሱውም መፃፊያ ፊደላትን የሚመለከት ነው፡፡ አሁን ኦሮሞዎች የሚገለገለገሉበትን የላቲን ፊደላት በሃገር-በቀል ፊደላት ለመተካት ተነጋግራችሁበት ይሆን? መልስዎ አሉታዊ ከሆነ፣ ብትነጋገሩበት ሸጋ ነው፡፡ ራሳቸው አውሮፓውያን ካልሆኑ በቀር በላቲን የሚጽፉት የራሳቸው ፊደል የሌላቸው በነጭ ቅኝ ግዛትወይም በባርነት የተገዙ ምስኪን ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ እኛ እኮ የራሳችን ፊደል የአለን የተከበርን እና የረቀቅን ሰዎች ነን፡፡ የግዕዝ የሚባሉት ሆሄያት የኛ አይደሉም እንደማይሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ከአሉኝም ተሳስተዋል፤ እልዎታለሁ፡፡ የግዕዝ ፊደላት የአማራው ወይም የትግሬው ብቻ ከመሰልዎትም አሁንም ተሳስተዋል፤ እልዎታለሁ፡፡ ጳሩ የነሱም ብቻ እንኳን ቢሆኑ ከባዕዳኑ የላቲን ፊደላት ይልቅ የሃገራችን  ሰዎቹ ሳይቀርበን ይቀራል ይላሉ?*

*የግዕዝ ፊደላት፣ የዛሬ* 3000 *ዓመታት የግዕዝ ቋንቋ የበላይነት ከመታወጁ በፊት የነበሩ፣ አማራና ትግሬ ከመፈጠራቸው አስቀድሞ የኖሩ ጥንታዊ ናቸው፡፡ ሃቁን ለመናገር፣ ለመፃፊያ እንዲመቹ አድርጎ እንደገና ያነጻቸው፣ የኦሮሞ፣ የአማራና የሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አባት የነበረው ታላቁ ንጉስ፣ ሊቀካህናቱና ፈላስፋው ኢትዮጵ ቀዳማዊ ነው፡፡ ቀዳማዊ ኢትዮጵ የኖረው የዛሬ* 4000 *ዓመታት ሲሆን ፊደሎቹ ከዛ ጊዜ በፊት ነበሩ ማለት ነው፡፡ ይህም የሚመሰክረው ፊደሎቹ የሁሉም ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ነው፡፡ አጋዝያን ከጋዛና ከእስራአል ተነስተው ወደ ኢትዮጵያ በፈለሱበት  ወቅት ቋንቋቸውን እንጂ ፊደሎቹንም ይዘው ለመምጣታቸው ማስረጃ የለም፡፡ ኢትዮጵ የኖረው ከነሱ መፈለስ* 1000 *ዓመታት አስቀድሞ ነበርና፡፡ የግዕዝ ፊደላትን ያመጡት አጋዝያን ናቸው ከተባለም አሁን የሁላችንም ሆነዋል፡፡*

*ከነዚሁ ከግዕዝ ፊደላት ጎን ለጎን የኦሮሞ ካህናትና ሊቃውንት የተገለገሉባቸው ሌላ እጅግ ጥንታዊ ፊደላትም ነበሩ፡፡-- "የሱባ ፊደላት" የተሰኙ፡፡ የመጀመሪያ የሰው (የሰብዕ) ልጆች ቋንቋ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ "ልሳነሰብዕ" ተብሎም ይጠራል፡፡ አሁን ያሉትን የግዕዝ ፊደላት ኢትዮጵ ያሻሻላቸው ከሱባ ፊደላት አውጣጥቶ እንደሆነ ይወሳል፡፡ የግዕዝ ሆሄያት ከግራ ወደ ቀኝ ሲነበቡ እንደሚታወቀው ሰባት ድምጾች ይሰጣሉ፡፡ የሱባ የፊደል ድምጾች ግን እስከ ዐስር ድምጾች ያሰማሉ፡፡ ይህን በማድረጋቸውም የሰውን ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮን እና የእንስሳትን ደምጾች ስለሚጋሩ የሱባ ቋንቋ እጅግ የበለጸገ ነበር፡፡ የምስራች! ጠፍተው የነበሩት የሱባ ፊደላት ተገኝተዋል፡፡ ለአብነት የሚሆኑ ቅጂዎች በኔ በራሴ እጅ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም ከስደት ያመለጠ የሱባ እና የ ግዕዝ መዝገበ ቃላት ግልባጭም በእኔ ዘንድ አለ፡፡ እነዚህ ሁሉ የጥንት ሊቃውንት አባቶችችን እና አናቶቻችን የተጠቀሙባቸው ናቸው፡፡ በ ሱባ ቋንቋ የተከተቡ እሸንክታብ (የ ሚገርመው "ልሳነሰብ" ም ይባላሉ፤) ሞልተዋል፡፡ ክታቦቹ ውስጥ ያሉት የማናውቃቸው፣ የድግምት ጽሁፎች የሱባ ቋንቋ ናቸው! በዚሁ በሱባ አሸንክታብ ላይ የተመዘገቡ ጽሁፎችም በሳጥኔ ስውጥ ይገኛሉ፡፡ ስለ ግዕዝም እንኳን እንነጋግር ካልን፣  የሚገርምዎት ነገር፣ እኔና እርስዎ አይነቱዎቹ የዛሬ ዘመን ተረናል የምንል ሰዎች  "የግዕዝ ፊደላት የኦሮሞኛ ቋንቋን ሊያስተናግዱ ይችላሉ፣ አይችሉም" እያልን ስንከራከር፣ ጥንታዊ አባቶቻችን በግዕዝ ፊደላት የረቀቁ እና የመጠቁ ሃሳቦችን ገልጸውባቸዋል፡፡ እኔ እጅ ውስጥ እንኳን ቢያንስ አንድ ሺ ዓመት ሊሆን የሚችል በግዕዝ ፊደላት የተከተበ ብራና ግልባጭ አለ፡፡ ይህን ሁሉ መረጃዬን በቅርቡ በማሳትመው የኦሮሞን እና የ አማራን ታሪ ክ በሚያወጋው የእንግሊዝኛ መጽሃፌ ላይ አስመሰክረዋለሁ፡፡*

*"ሱባ"ን በሚጠቅስ ግን፣ "ለመሆኑ ሱባ የሚባል ነገር አለን? ወይስ ነበረን?" ብሎ የሱባን መኖር ለሚጠራጠር ኦሮሞ ግን፣ ለሱባ መኖር እሩቅ ሳንሄድ ዋናው ምስክር እርስዎ ራስዎ ነዎት፡፡ ምክንያቱም፣ ውድ ዶክተር በያና ሱባ ሆይ! ይህን ቃል ርስዎ ራስዎ ተሸክመውት አሉና! ወይም ይህ ቃል ርስዎን ተሸክሞ ይዞራልና! ኦሮሞው አያቶ ለአባቶ ይህን ስም ሲያወጡላቸው የቃሉን ትርገም እና ታሪክ  ጠንቅቀው ሳያውቁ እንዳልቀሩ አያጠራጥርም፡፡ "ሱባ" ተብለው በዚሁ ስም የተጠሩት አባቶም የስማቸውን ትርጉም አጥርተው እንደሚያውቁ አያጠያይቅም፡፡ የ "ሱባን" ትርጉም እና ታሪኩን የማናውቀው እኛ ጥራዝ-*

***ነጠቆቹ የተማርን ተብዬዎቹ እንጂ እያት ቅድመአያቶቻችን አይደሉም:: የፈረንጅ ዲግሪ አይኑራቸው እንጂ እነሱ በሃገራቸው እውቀት የረቀቁ ናቸው:: ለማንኛውም የ "ሱባ"ን ታሪክ እና ትርጉም እኔና ርስዎ አወቅነውም እላወቅነው፣ አባቶቻችን እንደዘገቡልን፣ የዛሬ 4000 ዓመት ይህን ቃል ለስም መጥሪያ አድርጎ የተጠቀመው አባታችን ኢትዮጵ ነው:: ይህም ኢትዮጵ የኦሮሞዎችም አባት ለመሆኑ አንድ ማስረጃ ነው:: ኢትዮጵ ሶስት ሴቶች ልጆች ወልዶ ነበር:: የአንደኛዋን ስም "ሱባ" ሲል ሰየመው:: የሱ የልጅ ልጅ የሆነው ኢትዮጵ ሁለተኛው ደግሞ እጡብ ድንቅ ከተማ ቆርቁሮ ስሟን "ሱባ" አለው:: በ ኬንያና በ ታንዛኒያ ደግሞ "አባሱባ" የተባሉ፣ ከኢትዮጵያ ሸሽተው የሄዱ ጎሳዎች አሉ:: ኢትዮጵ አስር ወንዶች ልጆች ወልዶ ነበር:: እነዚህ አስሩ ዛሬ ኢትዮጵያውያን ተብለው የሚጠሩት ሁሉ ሕዝቦች አባቶች ናቸው:: ከውንዶች ልጆቹ አንዱን ኢትዮጵ "ቶላ" ብሎ ጠራው:: የኔ የኦሮሞው እጎቴ (የአባቴ ወንድም) ስሙ "ቶላ" ነበር:: ኢትዮጵ የኦሮሞዎችም አባት ለመሆኑ ይህም ሌላ ማስረጃ ነው:: ክቡር ዶክተር በያና ሱባ ሆይ፣ ይህ የኩራትና የክብር ጉዳይ ስለሆነ የላቲኑን ፊደሎች ቋንቋ ለሌላቸው ድሆችና በቅኝ ለተገዙ አሳዝኞች ትተን ጠቢባኑ አባቶቻችን በፈለሰፉት በራሳችን በሱባ ወይም በግዕዝ ፊደላት እንጽፍ ዘንድ የተገባ ነው:: ስለዚህ ርስዎና የአዲሱ ድርጅታችሁ የኦሮሞ ባልደረባዎችዎ ይህን ጉዳይ አበክራችሁ አስቡበት:: የእናንተ መልካም ፍቃድ ከሆነ፣ በዚህ በኩል እኔም ልተባበራችሁ ዝግጁ ነኝ:: በጄ ውስጥ የአሉትንም ስነዶች ለማሳየት ወደ ኋላ አልልም:: ከኢትዮጵ ጀምሮ የነበሩት አባቶቻችን የእኛን በላቲን መጻፍ ቢያዩ ኖሮ አፍረውና አዝነው "እዬዬ!" ብለው ማልቀሳቸው አያነጋግርም::***

***የዳር ድንበሩና የባንዲራውም ነገር እንደ እዛው ነው:: የኦርሞዎች፣ የአማራና የሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አባት ኢትዮጵ እና ልጆቹ ያቀኑትና ያስፋፉት ምድር በመላው አፍሪካ ብቻ የነበረ ሳይሆን ወደ አረብያ፤ መካከለኛው ምሥራቅና እሥያም የዘለቀና የዘለለ ነበር:: እንዳውም መላው አፍሪካ "ኢትጵያ" ተብሎ ይጠራ ነበር:: ሚል፣ ሚል እየተሸራረፈ ሄዶ አሁን ያለው ኩርማን መሬት ብቻ ተርፏል:: እሱውም ቢሆን አሁንም በየአቅጣጫው እይተሸረሸረ ነው:: የሆነ ሆኖ ሁላችንም የኢትዮጵ ልጅ እንደመሆናችን መጠን አገራችን መላዋ ኢትዮጵያ እንጂ ኦሮምያ ተብላ በቀደም እለት የተጠራች ጭራ-ቀንዱ የት ጋ እንዳለ ያልተረጋገጠና የተወሳሰበ ኩርማን መሬት አይደለችም:: ስለዚህ "ኦሮምያ" በተባለችው ጠባብ ስፍራ ከመኮራመት ይልቅ በሁዳድዋ ኢትዮጵያ ወርድና ስፋት ላይ መቦረቅ ይገባናል:: ክብርነትዎ በዚህ የብልህነት እሳቤ እንደሚስማሙ አልጠራጠርም::***

***የሃገራችንን ባንዲራ "ሠንደቅአልማ" ሲል ሰይሞ የዛሬ 3400 ዓመታት የፈጠራት ስመ-መንግሥቱ ሠንደቅአልማ ተብሎ ይጠራ የነበረው ግንደዘራችን የኢትዮጵ ሽንት አጼ እስያኤል ነው:: የነጻነት አርማና የኢትዮጵያዊነት ክብር ተብላ በንጎሦች ሰረገላዎችና ቤተመንግሥቶች፣ እንዲሁም በጦር ሜዳዎች ትውለብለብ ብሎ አዘዘ:: እሱ የመረጣቸው ቀለማት አረንጓዴ፣ ቢጫና ሰማያዊ ነበሩ:: በሰማያዊው ፈንታ አሁን ቀይ ተተክቷል:: ስለዚህ የኦሮሞ ዝርያ የሆንን ሁሉ፣ የኢትዮጵያ ባንዲራ የኛም መሆንዋን አውቀን በኩራት ልናውለበልባት ይገባል:: አደራዎን-- ርስዎ እና ተባባሪዎችዎ ሆናችሁ የባንዲራዋን ነገር አስቡበት:: ይህች የነፃነት ሰንደቅአላማ አየር ላይ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ አያሌ የኦሮሞ ጀግኖች ባለፉት 3400 ዓመታት በደማቸው መሥዋዕትነት ከፍለውላታል:: እኛ የአሁኖቹ ትውልድ ይችን ሠንደቅአላማ አክብረን መውደድና እሷ በነፃነት ዐየር ላይ ትውለበለብ ዘንድ በተራችን ራሳችንን መሰዋት ግዴታችን ነው::***

***እላይ ከተጠቀሱት ጉዳይዎች የማያንሰው ወይም የሚልቀው የኦሮሞውችና የአማራዎች ግንኙነት ነው:: ኦሮሞዎችና አማሮች የመነጩት የዛሬ 3600 ዓመት አካባቢ ደሸት ከተባለ ነቢይና ፈላስፋ አብራክ ነው:: ቦታውም ጎጃም ነበር:: ደሸት ጂማን፣ ማጂን፣ መደባይን እና መንዲን ወለደ:: ጂማ ማራን (አማራን) እና ጃማን (ጃማካንስ ወይም ጃሜካንስ የጃማ ልጆች ናቸው፣) ወለደ:: መደባይ፣ ጂማና መንዲ የኦሮሞዎችና የሌሎቹ ኢትዮጵያውያን አባቶች ሆኑ:: ኦሮሞ "ኦሮሞ" መባል የጀመረው የዛሬ 3000 ዓመት፣ በቀዳማዊ ምኒልክ***

ዘመንመንግሥት ነበር። ከዛ በፊት ግን ዋናዎቹ ኦሮሞዎች መደባይ ተብለው ይጠሩ ነበር። አሁንም ድረስ በዚህ ታላቅ ስም የሚጠሩ ኢትዮጵያውያን በጎጃም፣ በጎንደር በትግራይና በሌሎችም ቀዬዎች ይገኛሉ። የዚህን ዝርዝር ወደፊት አቀርበዋለሁ። ኦሮሞዎችና አማሮች ከውጭ ሃገር አልፈለሱም። ጎጃም-ፈለቅ፣ ኢትዮጵያ-በቀል ናቸው። ኦሮሞዎች የኢትዮጵያን ዳርድንበር ዘለው የመጡ ፈላስያን ወይም ወራሪዎች ናቸው፣ የሚባለው ነጭ ውሸት ነው። ርግጥ ኦሮሞዎች ሃገርና ጀብድ ፍለጋ ከኢትዮጵያ እየተነሱ መላዋን አፍሪካ እያሰሱ የተወሰኑት ወደ ኢትዮጵያ እንደ ገና ይመለሱ ነበር። አንዳንዶቹ ደግሞ እዛው እሄዱበት ስፍራ ተመቻችተው ይቀሩ ነበር። ከሃገር ወጥተው ከቀሩት ከእነዚህ የኦሮሞ ዝርያዎች መካከል በኬንያ የሚኖሩት የኪኩዩና የማሳይ ጎሳዎች እና ርስታቸውን በሩዋንዳ ያደላደሉት ቱትሲዎች ይገኙባቸዋል። በማዳጋስካርም ቀልጠው የቀሩ ኦሮሞዎች አሉ። ለመደምደም ያህል፣ ኦሮሞዎችና አማሮች እንደሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ካንድ ደም የተቀዱና ካንድ አጥንት የተቀመሙ ናቸው። ይህን ሃቅ ግንዛቤ ውስጥ በመክተት ያለፈውን አለመግባባትና ግጭት ወደ ጎን ትቶ የወደፊቱ ህብረት፣ ፍቅርና ሰላም ላይ ማተኮር ይገባል።

በመጨረሻም፣ ርስዎን እና ድርጅትዎን የምመክራችሁ፣ እውነተኛው የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ፣ የዘር ሃረግና ባህል እንደገና ተጤኖ ይታወቅ ዘንድ አንድ የጥናትና የምርምር ማዕከል ወይም ተቋም እንድታቋቁሙ ነው። ይህም ማለት፣ የፖለቲካው ሥራ እንደተጠበቀ ሆኖ ነው። ይህ ተቋም፣ እውነቱን ከውሸቱ፣ ሃቁን ከተረቱ፣ ፈንጠዝያውን ከገሃዱ እውነታ ለይቶ የአእምሮ ውዥንብርን ያበናል፣ ያተናልና። ከዚህ ተቋም ተግባር አንዱ ማንነታቸውን የተወናበዱትን ኦሮሞዎች እውነተኛ ማንነት፣ ማለትም ኢትዮጵያዊነታቸውን እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው። በሚኖሶታ፣ በሌሎቹ ዩናይትድ ስቴቶች፣ በካናዳ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በአፍሪካ እና በኢትዮጵያም ጭምር የሚኖሩ በርካታ ኦሮሞዎች ከዚህ ቀደም "ኢትዮጵያውያን አይደላችሁም፣" ተብለው፣ ሃሰት ተነግረው፣ የማንነት ቀውስ (አይዴንቲቲ ክራይዚስ) እንደደረሰባቸው እሙን ነው። ይህን የማንነት ቀውስ ማስተካከል እንጻውም የድርጅታችሁ ቀዳሚ ተግባር መሆን አለበት። ይህ የማንነት ቀውስ ባሰቸኳይ መፍትሄ እስካላገኘ ድረስ ለሥራችሁ እንቅፋት ይሆንባችኋልና። ከዚህ በተረፈ፣ አዲሱ አቋማችሁና ግንባራችሁ ለኦሮሞ ሕዝብ፣ ብሎም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሰላምና እድገት እጅግ ጠቃሚ ናቸውና በርቱባቸው። በዚህ በተቀደሰ አላማችሁ ውስጥ እግዚአብሄር ገብቶበት ይርዳችሁ። ያለ እግዚአብሐር እርዳታ የሰው ድካም ሁሉ ከንቱ ነውና።

ዶ/ር ፍቅሬ ቶለሳ ጂግሳ፣
ዘብሄረ ኢትዮጵያ፣
ኢልማ ኢትዮጵ ንጉሠነገሥት ዘ ኢትዮጵያ፣
ኢልማ ደሸት፣ ነቢይ፣ ፈላስፋ፣ ሊቀካህን፣ ወ ንጉሠ ጎጃም።

እኤአ ግንቦት 24 ቀን 2013፣
ካሊፎርንያ

ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ፣ ጂግሳ፣ በ lulu.com or Amazon.com የሚገኘው የ **The Hidden and Untold History of the Jewish People and Ethiopians** ደራሲ ነው።

ለደራሲው አስተያይት መለገስ ካማረዎ በ **ftolossa@aol.com** ኢሜል ያድርጉለት። ጊዜ ካለው ይመልስልዎታል። ዌብ ሳይቱን ለመጎብኘትና አንዳንድ ጽሁፎቹን ለማንበብ ካማረዎ ወደዚህ ይሂዱ.. **Fikretolossa.com**




# ዶክተር በያን ኤች አሶባ ለዶክተር ፍቅሬ ቶሎሳ ግልጽ ደብዳቤ የላኩት መልስ ትርጉም - ይነጋል በላቸው

**ዶር. በያን አሶባ**

ውድ ዶክተር ፍቅሬ ቶሎሣ /ቶለሣ

በስሜ አድራሻ የላኩት ግልጽ ደብዳቤ በበርካታ ድረ ገፆች በወጣበት ወቀት እኔ ጉዞ ላይ ነበርኩ፡፡ በዚያም ምክንያት ወዲያውኑ መልስ መስጠት በምችልበት ሁኔታ ላይ አልነበርኩም፡፡ በዚህ በምጽፍልዎ የደብዳቤዎ ምላሽ እኔን ስለሚመለከቱ ነጥቦች ብቻ አነሳለሁ፡፡ የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግምባር ስለአጠቃላዩ የደብዳቤዎ ይዘት መልስ ይሰጥዎታል ብዬ አምናለሁ፡፡

ውድ ዶክተር ፍቅሬ

አስተያየቴን መጀመር የምፈልገው በዚህ ግልፅ ደብዳቤዎ የአያትዎን ስም እንዴት ሊጨምሩ እንደፈለጉና ይህ ያልተለመደ አካሄድ ያጫረብኝን ስሜት በማስቀደም ነው፡፡ አቅም በፈቀደ በርካታ የጽሑፍ ሥራዎችዎን ለመመልከት ሞክሬ ሁሉም ‹ፍቅሬ ቶሎሣ› እንደሚሉ አረጋግጫለሁ፡፡ ይህም አያትዎን ያለመጨመር የአጻጻፍ ይትበሃል እ.አ.አ በ1983 በብሬመን ዩኒቨርስቲ ለዶክትሬት ዲግሪዎ ማሟያ ያቀረቡትን ጹሑፍ ጨምሮ በሌሎች በርካታ ተከታታይ ጽሑፎችዎ አልተስተዋለም፡፡ በፌስቡክዎም የአያትዎ ስም አልተገለጸም፡፡ .እኔ እስከማውቀው ድረስ የራስዎን ስም ፍቅሬ ቶላሣ (Tolassa, not ከዚህ በፊት ይጠቀሙበት ነበር እንደሚባሉት Tolossa!) ብለው መጻፍ ብቻ ሣይሆን ‹ጂግሣ› የሚለውን የአያትዎን ስም ተጠቅመው የጻፉት በዚህ ግልጽ ደብዳቤዎ ብቻ ነው፡፡

እርስዎም እስካሁን ወደጎን ትተዋቸው እንደነበረው ሁሉ አሁን ‹ጂግሣ›ን ባሉበት እንዲያርፉ ለቀቅ እናድርጋቸውና አዘውትረው በሚጠቀሙበት ቶሎሣ/ቶለሣ በሚለው የአባትዎ ስም ላይ ትኩረታችንን እናውል፡፡ ‹ቶሎሣ› የሚለው ስም ‹ቶሎ› ከሚለው የአማርኛ ቃል ተወስዶ ኦሮምኛ እንዲመስል ‹ሣ›ን በመጨመር የተበጀ ቃል ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ በሌላ በኩል ‹ቶላሣ› ከኦሮምኛው ‹ቶላ› የተገኘ እንደሆነ በርግጠኝነት ዐውቃለሁ፡፡ በዚህም ሆነ በዚያ ስምዎን በሁለት መንገድ እየጻፉ ሁለት ተቃራኒ ማንነቶችን ለመላበስ መፈለግዎን መረዳት አይገድም፡፡ ይህን በማድረግ በአማራነትና በኦሮሞነት የማንነት አጥር ላይ ፊጥ ማለት ተመኝተው ከሆነ መንገዱን ጨርቅ ያድርግልዎ፤ በአራዶች አነጋገር ‹ይመችዎ!›፡፡

ሊሆኑት ወይም ሊጠሩበት በሚፈልጉት ስምም ይሁን ማንነት የመጠራት መብትዎን ሙሉ በሙሉ አከብራለሁ፡፡

የኔ ጥያቄ ይሄውልዎ፡- እኔ የርስዎን የፈለጉትን የመሆንና በፈለጉት የመጠራት መብት ሳከብርልዎ ለኔስ ይህን መብት ለምን ይነፍጉኛል? ስሜ Bayyanaa Suba አይደለም፡፡ ስሜን ‹Beyan Asoba› ከሚለው ውጪ በሌላ መልክ በፍጹም ጽፌ አላውቅም፡፡ ይህ የሰጡኝ አዲስ ስያሜ አባል የሆንኩበትን የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግምባርን በአንድ ወይ በሌላ መልክ ለመንካት ካልሆነ በስተቀር እኔን በተመለከተ ያወጡልኝ ስም ሊሆን ይችላል ብዬ መቀበል ያቅተኛል፡፡ በግልጽ እንደሚገባኝ ለፖለቲካዊ ዓላማዎ ሲሉ ይህን አዲስ ስም ፈልስፈው ለኔ የሰጡኝ ይመስለኛል፡፡

ለፍጡሮቻቸው ስም ማውጣት የሚቻላቸው ፈጣሪዎች ብቻ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ወላጆች ለልጆቻቸው የተለያዩ ስሞችን እንደሚያወጡ ሁሉ የመኪና ፋብሪካዎችም ለምርቶቻቸው የተለያዩ ስሞችን ይሰጣሉ፡፡

እንደመጥፎ ዕድል ሆኖ ለኛ ለኦሮሞ ሴቶችና ወንዶች ልጆች የስቃይና የውርደት ምክንያት ሆኖ አበሣና መከራ ያሳየን የነበረው የሕይወት መሪር ተሞክሯችን ስማችንን እንድንቀይር ትምክህተኞች (አማሮች?) ያደርጉብን የነበረው ጫና ወይም የማስገደድ ተግባር ነው፡፡ ኦሮሞ የሚለው ብሔራዊ መጠሪያችን ከማንኛውም መዝገብ ተፍቆ በርካታ አንቋሻሽ የፍካሬ ትርጉሞች በተለጣጠፉለት ስያሜ እንድንጠራ ተገድደን ነበር፡፡ ተማሪ ልጆቻችን ሳይቀሩ የተዋጣለት ኢትዮጵያዊ መሆን ይችሉ ዘንድ ስሞቻቸውን (ወደ አማራ ስሞች) እንዲቀይሩ በመምህሮቻቸው የሚገደዱበት ሁኔታም ነበር፡፡

በዚያች ሀገር ውስጥ ዋናው የፖለቲካ ማጠንጠኛ ግለሰቦች በቅድሚያ ኦሮሞነታቸውን፣ ሲዳማነታቸውን፣ ወላይታነታቸውን፣ ከምባታነታቸውን፣ ሃዲያነታቸውን ወዘተ. እንዲገድሉና በውጤቱም ኢትዮጵያዊ የሚባል የጋራ ማንነት መገለጫ እንዲኖራቸው ጥረት ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ኦሮሞነትና ኢትዮጵያዊነት አብረው ሊሄዱ ካልቻሉ ምርጫው ሁለት ነው፤ አንድም የእርስዎን ኢትዮጵያዊነት ባፍንጫችን ይውጣ ብለን መተው፣ አለበለዚያም በነበረው አካሄድ ነጻነትን ተነጥቀን እንደጥንቱ እያለቀስንና እየተሰቃየን መኖር፡፡

ለእርስዎና መሰሎችዎ በሚገባ ግልጥ አድርጌ ልነግራችሁ የምፈልገው አንድ ነገር አለኝ፡፡ ያም ኦሮሞዎች ማንነታቸውን ክደው በሚጣልባቸው የራሳቸው ያልሆነ ማንነት የሚንበረከኩበት ጊዜ አልፏል ወደፊትም አይመጣም፤ በዚህ ዕርማችሁን አውጡ፡፡ ኦሮሞነትን የሚጋፋ ኢትዮጵያዊነት አንቀበልም፤ ይህ ኢትዮጵያን ከኦሮሞ የማስቀደም አካሄድ እስካልቀረ ድረስም ትግላችን ይቀጥላል፡፡ ምርጫው የእርስዎና የቢጤዎችዎ ነው፡፡ እኛን ከነኦሮሞነት ማንነታችንና ከሌሎች ተዛማጅ መብቶቻችን ሙሉ በሙሉ መከበር ጋር ትቀበላላችሁ ወይም ከአደንቋሪ የኢትዮጵያዊነት ስብከታችሁና ከኢትዮጵያ አንድነታችሁ ጋር ጥንቅር ብላችሁ ልትቀሩ ትችላላችሁ፡፡ በኦሮሞዎች መቃብር ላይ፣ በሲዳማዎች መቃብር ላይ፣ በወላይታዎች መቃብር ላይ፣ በከምባታዎች መቃብር ላይ፣ በሃዲያዎች መቃብር ላይ፣ ወዘተ. የኢትዮጵያን አንድነት ለመገንባት ሲቋምጡ አንድ ዓይነት የሞራል ጉድለት አይታየዎትም ይሆን? ይህ

ዓይነቱ ጉዞ መጨረሻው የማያምርና ከቆመለት ዓላማ የተለዬ መጥፎ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል መገንዘብ እንዴት አቃተዎት? ይህ ዓይነቱ ኢምክንያታዊና ኢሞራላዊ የጥፋት መንገድ በመጨረሻው ስክነትንና ማስተዋልን ተላብሶ የሁሉንም በግዛቲቷ የሚኖሩ ወገኖች ፍላጎት ባማከለ ሁኔታ ሁሉንም የሚወክል ማንነት እንደሚያብብ ታላቅ ተስፋ አለኝ፡፡

በመጨረሻም በዚህ ራስ ምታት የሚለቅ አስቸጋሪ ጉዳይ ዙሪያ ይህ የአጻፋ መልሴ የመጀመሪያየም የመጨረሻየም እንደሆነ ልገልጽልዎ እወዳለሁ፡፡

በያን ኤች አሶባ (Beyan H. Asoba 5/29/13)

---

ከ‹ተርጓሚው› የተሰጠ አጭር አስተያየት

1. በአማርኛ ለተጻፈ ግልጽ ደብዳቤ በእንግሊዝኛ መልስ መጻፍ ምን ማለት ነው? ዶክተሩ ከጋና ነው ወይንስ ከእንግሊዝ የተገኙት? እዚሁ ከቅኝ ገዢዋ ኢትዮጵያ ውስጥ አልተፈጠሩ ይሆን? (ኢሣይያስና መለስ ነፍሳችሁ አይማር - ጥቁር ውሻም ውለዱ!) ዶክተር በያን ከአማርኛና ከእንግሊዝኛ የትኛውን አጣርተው ሊናገሩ ቋም ሊጽፉበት እንደሚችሉ በእንግሊዝኛ በጻፉት መልሳቸው በውል ተረድቻለሁ፤ ታዲያ አማርኛ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ለመግለጽ አውሮፓና አሜሪካ ድረስ ሄደው ለምን ትዝብት ውስጥ ይገባሉ?

2. የኢሣት የተለያዩ ባንዲራዎችን በኢትዮጵያ ስም ማስተናገድ ምን ማለት ነው? በጣም ይታሰብበት፤ በልክ ያልተያዘ ፍቅርና ጥላቻ መዘዝ አለው፡፡ ስንወድም ስንጠላም፤ ስንቀርብም ስንርቅም በምክንያት ይሁን እንጂ በስሜት አይሁን፡፡ የኢትዮጵያ ባንዲራ እንኳንስ ለአንድ ሕዝብ ለመላው ዓለም በቅቷል - የሌሎች ሀገራትን በተለይም የአፍሪካውያንን ባንዲራዎች ተመልከቱ፡፡ እኛ የምንጸየፋትን አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለማት ባንዲራ ከእኛ እየኮረጁ በተለያየ አቀማመጥ ይጠቀሙባታል፤ ነፈዞች ደግሞ የገዛ ባሏን የጎዳች መስሏት ገላዋን በጋሬጣ እንደሸነተረችው ሞኝ ሚስት እየሆኑ ያስቁን ይዘዋል፡፡ አትለማመጡዋቸው፤ ይልቁንስ የራሳችንን ሥራ እንሥራ፤ እውነትና ግልጽነት ያልተገባ ይሉኝታንና ፍርሀትን ያስወግዳሉ፡፡ እውነቱን ልባችን እያወቀው አንደበታችን በሀሰት ማባበልን ይተው፡፡ ለየትኛው ጊዜ...

የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁንልኝና በዚህ ጉዳይ ሰፋ ባለ ሁኔታ እመጣበታለሁ፡፡ በየወንዙ እንደሚማማል የማይተማን ጓደኛ ለማያዛልቅ ስትራቴጂ አንድ ጠረጴዛ ዙሪያ በአካል የተቀመጡ መስለው በምናብ ግን ተራርቀው መቀመጥ የሚያዋጣ አይደለም፡፡ እያፈረሱ ግንባታ የለም፤ እየጠሉ አንድነት የለም፤ የሚጸየፉህን ልመናና ልምምጥ የለም፡፡ የደነዘ አስተሳሰብ በምንም ዓይነት ሣሙና ቢታጠብ አይነጻም፡ ዐውቆ የተደበቀን ቢጠሩት አይሰማም፡፡ በጠላት ተቀፍቅፎ በበጎች ጋጣ ውስጥ የመሸገ ቀበሮና ተኩላ በልምምጥና እውነትን በመሸፈን በሚደረግ ልመና በረቱን ለቅቆ አይወጣም፤ የነገ ሰው ይበለን፡፡

# Why not Greater Oromia Instead of Ethiopia? A Response to Dr. Fikre Tolassa's Open Letter

(Dr. Fikre Tolossa)

I read an open letter written by Dr Fikre Tolassa ( http://www.gadaa.com/Beyana-Suba-1.pdf ) directed to Dr Bayan Asoba of the ODF and also saw the different responses from few Oromo nationalists including the one written by Dr Bayan himself. It is really an interesting discussion. I couldn't manage to ignore this discussion and to refrain from airing my own opinion in public for I used to write on such either pseudo- or true histories of the Oromo, the other Cushites and the Abyssinians now living in Ethiopia. Let me express my view regarding Dr Fikre's open letter. I don't belong to those who totally dismiss his view, but I do have certain concerns and a criticism in some areas of his writting.As I first heard Dr Fikre speaking and as I read his opinions, my reaction was: "here is a modern neo-Debtera carrying Oromo name and propagating the same old fictions and legends of the Abyssinians". I think he was also a bit like this at the beginning. For instance he used to write that the Oromo are who "expanded in the sixteenth century towards north and occupied Amhara territories":

"… The Amhara were not lucky enough to live in peace. Shortly after the Islamic wars were over, they engaged in a war with their other countrymen, the Oromo, who had started expanding into their territories in the 1520s when the Amhara were busy with their Muslim brothers. Compared with the Tigre, the Amhara lived in the most fertile regions of Ethiopia. Initially, the different Oromo tribes fought the Amhara wherever they happened to be, looking for ideal grazing lands for their cattle…." ( http://fikretolossa.com/FILES_ARCHIVE/POLITICS/Tigrean%20Members%20&%20Supporters.mht )

Thanks to the Oromo liberation struggle, now he is writting that the Oromo were/are the indigeneous people in this part of the globe and many Abyssinian scholars unwillingly started to entertain this fact. We need to congradulate Dr Fikre for his change of mind and for being ready to learn from new facts he ever get. I am not a historian and can not falsify or verify his current narration about history of the Oromo, but I can say one thing. His new version of the Oromo history is better than what the old Abyssinian Debteras used to write. They tried to denigerate the Oromo and regarded this great nation as alien to the North East African region, whereas he glorifies and confirms that the Oromo nation is the back bone of the region.

When it comes to the geneology he tries to tell us, I don't want to say it is a fabel, but I would like to recommend Oromo scholars with conscious mind of Oromo nationalism to engage him, find out the fact and try to consider his perspective in writing Oromo history from Oromo point of view. As I could understand from one of his hitherto opinions, his information is based on one discovery of a very old literature in Nubia. He once wrote: "… This information is based on on my reading of Ethiopian history and Metsehafe Djan Shewa, (an ancient Ethiopian manuscript in Geez discovered by Meri Ras Aman Belay, in the ruins of an Ethiopian church in Nubia, a part of the Ethiopian Empire) which has been, translated into Amharic, abridged and published as Metsehafe Subae by the discoverer himself… " http://fikretolossa.com/FILES_ARCHIVE/MISCELANEOUS/A_BRIEF_NOTE_ON_THE_ORIGIN_OF_THE_AMARA_AND_OROMO[1]_2.pdf )

According to this finding, the geneology speaks more for the Cushites, to which the Oromo is the main stalk and from which the other Cushitic nations of the region seem to be differentiated. The name Amara was derived from Mara (an Oromo term), "one of the sons of Deshet". A-Mara means, according to his assertion, children of Mara. I think the logic behind this derivarion is, if we take the geneology at face value, that Amara are the children of one of the Oromo (Cushite). This assertion supports the claim of some historians that the

Abyssinians are the self-denying Cushites whose priori identity could be either Agaw, Oromo or other Cushitic nations. I think it is better to say that Agaw and Oromo were brothers and the Abyssinians are the converted Cushites, who in due time changed their identity by accepting the system of both Aristocracy and Theocracy and claimed to be from Semetic origin, just to distance themselves from the common people.

Coming to the appeals, which Dr Fikre directed towards Dr Bayan, it seems that Dr Fikre lacks a necessary sensitivity regarding the Oromo national liberation struggle of the last more than 150 years. Disregarding whether the Abyssinians and the Oromians are biologically related or not, the fact on the ground tells us that the Abyssinian elites were and still are the enemies of the Oromo people because of the crime they used to do and are still doing. Whatever name we give to the oppression (colony, domination, exploitation, dictatorship, empire buildung and -keeping, tyranny, fascism…etc), the Oromo people are in a bitter struggle to get back our freedom by any means. Dr Fikre seems to have a sympathy towards keeping the empire at any cost, instead of adressing the Oromo grievance. To this end, he tries to instrumentalize his knowledge of history, be it pseudo- or true history.

This attitude of him is well reflected in the three demands he made: change of the alphabet used in writing Afaan Oromo from latin to saba; persuading Oromo to strive further in order to keep unity of "greater Ethiopia" by abandonig a "little Oromia"; wishing the Oromo to love the curent Ethiopian flag; and asking the Oromo to accept Ethiopian identity rather than being proud of their Oromo identity. These demands actually faced furious resistance from almost all Oromo nationalists who read his open letter. They percieved his opinion as a mischieve calculated from the Abyssinan camp to weaken the Oromo national liberation struggle and to possiblly reverse the victories achieved up to now.

Unfortunate to Dr Fikre and those who do have the same stand like him, the Oromo struggle has reached at the very irreversible stage. Using latin alphabet has got not only linguistric value, but also political meaning. Simply put, it is one of the the ways used to distance the Oromo national identity from that of the oppressors. Also a flag has got both emotional and political dimention. One can not love the symbol of an enemy at any battle field. Most of Oromo nationalists, who fought and struggled against the Abyssinian empire had to fight against forces carrying this flag. That is why it is wrong to expect Oromo nationalists to love and wear Ethiopian flag as Dr Fikre seems to do.

Regarding "little Oromia vs greater Ethiopia" he mentioned, I would like to recommend Dr Fikre and all who love the empire to rename the country they want to save as Oromia. When we look at the version of history he wrote, the whole empire can be called Oromia. Just as their Addis is our Finfinne, their Ethiopia is our Oromia. Because of the fact that the name Ethiopia is contaminated by the meaning given from the Greeks (burnt face, which is almost the same to the N-word used against blacks) and by the content given from the Abyssinians (making Ethiopia equivalent to Abyssinian empire's system of domination, excluding as well as exploiting the Oromo and the other nations), this change of the name is mandatory, if we really want to live together. That is why I asked in the title of this opinion: why not you accept greater Oromia, rather than asking the Oromo to join you in loving immiye Ethiopia? Surprisingly, the Abyssinian elites who tried to exclude the Oromo from the Ethiopian identity are now doing every thing under the sun in order to persuade us to accept this same identity. The response of Dr Bayan regarding this attempt is very precise and to the point:

"… I want to make one thing perfectly clear to you and your likes. The days when Oromos had to endure self-abnegation are over and shall never return. We have rejected the Itophiyawinnet that is the antithesis of being an Oromo and shall continue to do so as long as this antithetical relationship is maintained. The choice is yours and your likes'. You either accept us with our identity and other rights fully respected or you kiss goodbye to your much vaunted Itophiyawinnet and Ethiopian unity. Can you not see that there is something immoral in trying to build Ethiopian unity on graves of Oromos, Sidamas, Walayitas, Kambatas, Hadiyas, etc .? Why do you refuse to recognize that this aspiration is ultimately counterproductive? I only hope that this irrational, immoral and ultimately destructive aspiration would give way to a more sober and fair articulation of an Ethiopian identity that is as an amalgam of the identities of the various nations inhabiting its territorial

space… ”

Simply put, I want to tell Dr Fikre and the others, who do have a similar attitude that the future of the empire will only be either to be transformed in to a genuine union/true federation as the ODF planned, the union which can be given the name “greater Oromia” if you agree or you will just face the inevitable emergence of the “littlle Oromia” in a form of an independent republic as the OLF is trying to achieve. Both you, the Abyssinians, and we, the Oromians, know very well that Oromia being occupied by Abyssinia and kept within Ethiopia will not last as long as you want. That is why we need to come to our senses and try to find a solution, in which we all do have a win-win compromise. Manipulating histories and legends is not what we have to do now. Important is a future oriented creative thinking, which can benefit all the nations in the empire. All the anti-Woyane forces (the pro-independence forces like the OLF, the pro-federation forces like the ODF and the pro-unity forces like the UDJ) ought to come together unconditionally and deal with the fact on the ground, instead of the ongoing day-dreaming about any sort of past legend or future utopia.

Last but not least, what ever our history is, there will be no compromise on the destiny of the Oromo nation. All nations in the empire do deserve an imperative freedom of their people and an optional independence of their land (based on the public verdict of the respective nations). The Oromo as a nation does have two alternatives after achieving the national liberation by our bitter struggle: either to have free Oromia within a union of nations in the region or free Oromia within the United Nations (UN). I think Dr Fikre and all the pro-unity forces need to realize this fact. As far as I am concerned, free “little Oromia” within a local union as planned by the ODF is only a temporary solution leading towards the free Oromia within the UN as envisioned by the OLF. For the Abyssinians to save the unity of the country forever, they have to approach the Oromo nation with a better idea than an independent “little Oromia”. That better idea can only be a transformation of the present Ethiopian empire to a future union of free nations called “greater Oromia”, of course with Afaan Oromo as the primary working language of the union and a flag of the union with mo’aa odaa, instead of mo’aa anbessa or mo’aa anbasha, at its center. May Rabbi/Waaqa help you, the Abyssinians, and us, the Oromians, to accept this reality!

Galatooma!

Read more

# ዶ/ር በያን አሶባ ለግልጽ ደብዳቤዬ ለሰጡት ምላሽ መልስ

## ውድ ዶ/ር በያን አሶባ

በቅርቡ ለጻፍኩልዎት ግልጽ ደብዳቤ የከተቡልኝን አጻፋ በኢትዮሜዲያ ድሕረገጽ አስፍረውት ዐየሁት:: የደብዳቤዎን ርዕስ እንደ አጤንኩት "እኚህ ሰው በጣም ትልቅ ናቸው፣ ቢዘገዩም መልስ ሡጡኝ:: እንግዲህ ስለሕዝባችን ዕጣ ፈንታ በቁም-ነገር ሊያነጋሩኝ ነው፣" በማለት አክብሬዎት ነበር:: ወደ ውስጥ ዘልቄ ሳስተውለው ግን ለካስ እርስዎ የሕዝባችንን ሕይወት የሚነካውን አንገብጋቢ ቁም-ነገር ወደ ጎን ትተው የእርስዎንና የእኔን ስሞች አንስተው እየሰነጣጠቁ ኖሯል የከተቡልኝ:: እኔም ሆንኩ የኢትዮሚዲያ አንባቢዎች እርስዎን ከሚያህል ትልቅ ሰው የጠበቅነው ይህን አልነበረም:: ይህም በመሆኑ "እኒህ ሰው ለግል ስማቸውና ክብራቸው ነው የሚቆረቆሩት ወይንስ ለታላቁ የኦሮሞ ሕዝብ?" ስል ራሤን ጠየቅኩ::

የሆነ ሆኖ ስምዎን አሳስቼ በመጻፌ ይቅርታ እጠይቃለሁ:: ስምዎን እንደዛ ብዬ የጻፍኩት እርስዎ እንዳሰቡት ሆነ ብዬ በፖለቲካዊ ምክንያት ወይም እርስዎን ባለማክበሬ ሳይሆን፣ ስምዎን ከዛ በፊት ሰምቼ ባለማወቁ ለጆሮዬ ባዕድ ስለ ነበር ነው:: ስምዎን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት ከሳምንታት በፊት በኢሳት ሬዲዮ ሲጠራ ነበር:: እርስዎም ቢሆኑ የእኔን ደብዳቤ ከማየትዎ በፊት እኔን ያወቁኝ አይመስለኝም:: የኢሳት ሬዲዮ አስተዋዋቂ ስምዎን ሲናገር ለጆሮዬ "በያና ሱባ" የሚል መስሎ ተሰማው:: "ሱባ" በሚለው ቃል ኢትዮጵ ልጁን የጠራበት ከመሆኑም በላይ እኔ እስከማውቀው ድረስ በጥንት ኦሮሞዎች ዘንድ የተከበረ ስም በመሆኑ በእውነቱ ሥምዎ መሰለኝ:: ስለ እዚህም "እኚህ ሰው የከበረ የጥንት የኦሮሞ ስም አላቸው፣ ስማቸውን ከሱባ ፊደላት ጋር አያይዤ ብናገር ይገጣጠማል፣" ብዬ ወደድኩት:: የሚያሳዝነው፣ ለካስ ተሳስቼ ኖሯል! በቃ ነገሩ ይኼው ነው:: የሚገርምዎት ነገር፣ "ሱባ" የተባለውን ለ 4000 ዓመታ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረውን የጥንት ስም እኔ እሩቅ ሄጄ ስፈልግ፣ ለርስዎ የጻፍኩልዎትን ደብዳቤ የ አነበቡ ጥቂት ሰዎች በ ስልክና በ ኢሜል፣ " ከአዲስ አበባ ወጣ ብለህ፣ ወደ ሆለታ መናገሻ ስታመራ፣ በስተግራ ተጠምዝዘህ ከሄድክ "ሱባ" የሚባል የኦሮሞ ሰፈር አለልህኮ፣" ብለው አበሰሩኝ:: ምናልባት እርስዎ ይህን ቦታ ያውቁት ይሆናል:: ከ 4000 ዓመታት በፊት ኢትዮጵ ለልጁ የሰየመው ስም አሁንም ድረስ መኖሩና በሆለታ አካባቢ የኦሮሞዎችን ቀዬ ስም ይዞ መገኘቱ የኦሮሞ ሕዝብ ከኢትዮጵ እና ከኢትዮጵያ ጋር አንድ ዐይነት ግንኙነት እንደ አላቸው ይመሰክራል:: የጥንት ኦሮሞ ሊቃውንት በሱባ ቋንቋ ይጽፉ ነበር ያልክዎትም ከዚህ ጋር የተሰናሰለ ነው:: የሱባ ፊደላት እና ከፊደላቱ በተጨማሪ የሱባ እና የግዕዝ መዝገበቃላት በድሮ ዘመን ተቀብረውበት በነበሩበት ስፍራ ከ 45 ዐመታት በፊት ስለተገኙ ስለ ሱባ ኢትዮጵያዊነትና ነባርነት የመረጃ ችግር የለም::

ስምዎን አስመልክቶ፣ ሀቁ ይሄ እላይ የተጠቀሰው ሳለ፣ ክቡርነትዎ ግን ብዙ ብዙ ክፉ ነገሮች በቁጣ አተቱ:: በስሜት ጎዳና እጅግ ርቀው ሄደውም መሪር ንግግሮችን ተናገሩ:: የአንድ ብሄር ሰዎች ተሰብስበው በእርስዎ ላይ ሴራ ያሴሩም አስመሰሉ:: ኢላማዎ እንድሆን በማይገባኝ በኔ ላይ የቃላት እሩምታ ተኮሱ:: የእኔ ዐይነቱ አንድ ግለሰብ ስምዎን አሳስቶ ስለጻፈ ብቻ ተበሳጭተው ስለ ተለያይቶ መኖር አስፈራሩ:: እኔም "እኚህ ሰው በቀደም እለት በኢሳት ሬዲዮ አብሮ ስለ መኖር አብስረው አልነበረም እንዴ? ከመቼው ሃሳባቸውን ለወጡ? የሃገር ጉዳይ እንዲህ በቀላሉ የሚለዋወጥ ነው እንዴ?" ብዬ ተደመምኩ::

ከዚሁ እኩል እኔን ያሳዘነኝ ግን፣ እኔ በኢትዮጵያዊነቴ እና በኦሮሞነቴ እጅግ የምኮራ የኢትዮጵያ ኦሮሞ ሆኜ ሳለ እኔን እንደ በርካታ ሰዎች ቆጥረው ማንነቴን በድፍረት በመለወጥ "እናተ አበሾች" ብለው እኔ በአልሆንኩት በአበሻነት አለአግባብ ፈረጁኝ::

“እሳቸው ለራሳቸው ስም እንዲያ እየተንገበገቡ እንዴት የእኔን ማንነት ለኔ ከመፈረጅ “አልፈው እስከነአካቴው እኔነቴን ይለውጡታል?” ብዬ ቅር ተሰኘሁብዎት፡፡ ስለ እኔ ይበልጥ ለማወቅ ከአሻዎት ግን፣ እኔ እንደ ሁሉም ኢትዮጵያውያን፣ ከኀያሉ ሊቀ-ካሕናትና ንጉሠነገሥት ከኢትዮጵ አብራክ የፈለቅኩና የኦሮሞ፣ የአማራ እና የሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አባት ከሆነው ከነቢዩ፣ ከካህኑና ከጠቢቡ የጎጃም ንጉሥ ከደሸት (ደሴትም ይባላል) የተገኘሁ ማንነቴን ጠንቅቄ የማውቅ ጅንን የኢትዮጵያ ኦሮሞ ነኝ፡፡ እንደኔ ዐይነት የሆኑ በሚሊዎኖች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ኢትዮጵያውያን እንደ አሉም አያጠያይቅም፡፡ እርስዎ በዲሞክራሲና በሰው ልጅ የመኖር መብት በእውነት የሚያምኑ ከሆነ የዚህ ዓይነቶችም ኦሮሞ ኢትዮጵያውያን መኖራቸውን ተቀብለው በሃገራቸው ላይ እንዲኖሩና ሃሳባቸውንም ያለ አንዳች ፍርሃት በነጻነት ለመግለጽ የሚያስችላቸውን ሰብአዊ-ሃርነት እንደማይነፍጓቸው አምናለሁ፡፡ እንደነዚህ ዐይነቶቹንም ኦሮሞዎች፣ “ትክክለኛውና የጠራሁት ኦሮሞ እኔ ብቻ ነኝና እናንተ ኦሮሞ አይደላችሁም፡” ይሏቸዋል ብዬ አላስብም፡፡ ሰው “እኔ ነኝ” የሚለውን ሁሉ የመሆን መብት አለው፡፡ እርስዎ “ኢትዮጵያዊ አይደለሁም፣” የማለት መብት እንደ አለዎት ሁሉ ማለት ነው፡፡ “ኢትዮጵ” የተባለ ታላቅ ሰው አንድ ጊዜ ገንኖ በዚች ዓለም ላይ ስለመኖሩ ግን ማስረጃው ምንድን ነው ከአሉኝ፣ እሩቅ ሳልሄድ ማስረጃውን አቀርብልዎታለሁ፡፡ ማስረጃውም፣ በድሮ ጊዜ መላው አፍሪካ በኢትዮጵ ስም “ኢትዮጵያ” መባሉ (ከ 300 ዓመታት በፊት ፈረንጆች የሳሉትን የአፍሪካ ካርታ ፈልገው ይመልከቱ፤) እና ሲል ሲል ያ ሁሉ ተቀንሶ፣ እንደጥንቱ ትልቅ ባትሆንም ዛሬም “ኢትዮጵያ” የምትባል ሃገርና “ኢትዮጵያውያን” የሚባሉ ሰዎች መኖራቸው ነው፡፡ አለዛ “ኢትዮጵያ” የተባለችው ሃገር በምን የተሰየመች ይመስልዎታል?

እርስዎ የእኔን ማንንት ከመለወጦም በላይ፣ እኔ ስሜን ”ቶላሳ” ብዬ ሳልጽፍ ጽፈሃል አሉኝ፡፡ በህጻንነቴ ትምህርት ቤት ስመዘገብ ስሜ በስህተት ወይም ሆነ ተብሎ የአባቴ ስም “ቶሎሳ” ተሰኝቶ ተጽፎ ነበርና ከትምህርት ቤት ጀምሮ እስከዛሬ ይህን ስም በየሰነዱ ላይ ተሸክሜው እዞራለሁ፡፡ አጠራሩን “ቶለሳ” ብሎ ለማስተካከል በተለያዩ ዘመናት በልቤ ባስብም ስሙን ለማስቀየር ህጋዊ ውጣ ውረድ ስለአለው በፓስፖርቴ፤ በዲፕሎማዬ፣ በመንጃ ፍቃዴና በሌሎች ሰነዶቼ ሁሉ ላይ ይሄው ስም ሰፍሮ ይኖራል፡፡ በኢትዮጵያውን የመገናኛ አውታሮች ላይ ግን በቀላሉ እንዳላስተካክለው የሚያግደኝ ነገር ስለሌለ ”ቶለሳ” እያልኩ አስተካክዬዋለሁ፡፡ አባቴም አያቴም ኦሮሞ መሆናቸውን አንዳንድ ሰዎች መጠየቅ ስለ አመጡ ደግሞ የአያቴንም ጨመርኩበት፡፡እርስዎ ግን እኔ ልብ ውስጥ የሚኖሩና በኔ እና እንደስማቸው ሰወለጋ ጀግና እና የተከበሩ በነበሩት በ ውድ አያቴ በ ጂግሳ መሃል ያለንን የፍቅር ልክ እሳቸው ወይም እኔ የገለጥኩልዎት ይመስል ለአያቴ ግድ እንደሌለኝ አድርገው በዘለፉ ጻፉብኝ፡፡ የአያቴን ስም ግን ያሰፈርኩት በመጀመሪያ ለእርስዎ በ ከተብኩልዎት ደብዳቤ ላይ ሳይሆን ከሱ ቀደም ብዬ ባለፉት ጥቂት ዐመታት በውይይት መድረኮች ላይና በቅርቡ በፈጠርኳቸው ግጥሞቼ ነው፡፡ አሁንም ቢሆን “ፍቅሬ ቶሎሳ” የተሰኘው ስሜ በዓለም-አቀፍ የደራስያን ሰነዶችና ኤንሲክሎፒዲያ ኦፍ አፍሪካን ሊትሬቸር በተባለው መጽሃፍ ውስጥ ስለገባ እና ከታዋቂ የአውሮፓና የአሜሪካ ደራስያን ስሞች ጋራ በተለያዩ መድበሎች ውስጥ ስለ አለ በዚሁ ስም ታውቄአለሁና፣ አሁን ልቀይረው ስለማልችል ለወደፊት በማወጣቸው መጣጥፎችና መጻሕፍት የተለመደውን “ፍቅሬ ቶሎሣ” ን ማስፈሬ አይቀሬ ነው፡፡ በ እኔ በኩል “ፍቅሬ ቶለሳ ጂግሳ” የተባለው ስም ለኦሮሞና ለአማራው፣ እንዲሁም ለሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ዘመዶቻችን የሚጠቅም የፍቅር ድልድይ ከሆነ “እሰየው! ይበል!” እላለሁ፡፡ ስምን ለሕዝቦች ፍቅር፣ ሠላም፣ ኅብረትና ብልፅግና ማዋል የተቀደሰ ተግባር ነውና፡፡ ከዚህ በተረፈ ግን ስሜ ላይ ማተኮር ምንም ፋይዳ የለውም፡፡ በዚህ ረገድ ፋይዳው መልእክቱ እንጂ መልእክተኛው አደለም፡፡ ስለዚህ እኔን ችላ ብለው፣ በግልጽ ደብዳቤዬ ላይ በሰደድኩልዎት መልእክት ላይ ቢያተኩሩልኝ ደስ ይለኛል፡፡

“ቶሎሳ” የተባለው ቃል ቢያንስ በወለጋ እና ሸዋ ኦሮምኛ ርስዎ እንዳሉት “ቶላሳ” ሳይሆን እኔ ከርስዎ በላይ ባላውቅም “ቶለሳ” ነው፡፡ ትርጉሙም “ቸርነቱ“ (የእግዚአብሕር?) ወይም “ደግነቱ” አንደማለት ነው፡፡ ከተሳሳትኩ እታረማለሁ፡፡ እውነቱ ግን፣ እዚህ ላይ እኔ ሳልሆን

እርስዎ የተሳሳቱ ይመስለኛል:: “ቶሎሳ” የተሰኘው ቃል በትክክል ያልተከተበ የኦሮምኛ ቃል እንጂ እርስዎ በግድ ፈጥረው ሊያደርጉት እንደጣሩት “ቶሎ” ከተሰኘው የአማርኛ ቃል ጋር፡ ምንም ዐይነት ግንኙነት የለውም:: “ቶሎሳ ” ወይም “ፈጥኖሳ” የሚል የአማርኛ ስም የለምና::

ኦሮሞዎች፣ አማሮች እና ሌሎቹም ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵ እና ከ ደሸት ወይም ከደሴት ስለመውረዳቸው ትንሽ ማስረጃ ለመቆንጠር ያህል፣ ደሸት ወይም ደሴት የዛሬ 3600 ዓመታት አካባቢ ለልጆቹ የሰጣቸው “መንዲ፣ ጂማ፣ መደባይ”፣ እና “ማጂ” የተባሉት ስሞች አሁንም ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ይነገራሉ:: ከዚህ በተጨማሪም፣ የዛሬ 800 ዐመት በሰሎሞን ሥርወመንግሥት ስም ነግሶ የኦሮሞን መንግሥት የመሰረተው ተስፋእየሱስ ወይም ይኩኖአምላክ፣ እናቱ የኦሮሞው የአዛዥ ጫላ ልጅ ጊፍቲ መንዲያ እንደነበሩ የታወቀ ነው:: እንግዲህ “መንዲያ” የሚለው ቃል የኦሮሞ መጠሪያ ሆኖአል ማለት ነው:: ይህም ቃል ከኦሮሞዎች፣ ከአማሮች እና ከሌሎቹም ኢትዮጵያውያን አባት ከ ደሸት ወይም ከደሴት ጋር የቀጥታ ዝምድና አለው ማለት ነው:: ደሸት ወም ደሴት ጎጃም (ጎዣም) ላይ በአንድ ወቅት ለመኖሩ ደግሞ ማስረጃው እሱ የኖረበትን ስፍራ በስሙ እስጠርቶ ያ ስፍራ አሁንም ድረስ ደሴት ተብሎ በጎጃም ጣና ሃይቅ ዙሪያ መኖሩ ነው:: ይህ የሱን ስም የተሸከመው ደሴት በአማርኛ ቋንቋ በውሃ የተከበበን መሬት መግለጫም ሆኖአል::

ይመኑኝ ዶ/ር በያን አሶባ፣ ኦሮሞዎች ሁሉ የኢትዮጵ ልጆች እና ኢትዮጵያውያን ናቸው:: ኦሮሞዎች ኢትዮጵያውያን ካልሆኑ ታዲያ ምን ሊሆኑ ነው? ባዕዳን መጤዎች ሊሆኑ ነውን? “ኦሮሞዎች ባዕዳን መጤዎች ናቸው” የሚሉ ኦሮሞዎች “ኦሮሞዎች በግራኝ አህመድ ጦርነት ጊዜ ከእስያ ፈልሰው በማዳጋስካር አድርገው ኢትዮጵያን የወረሩ ናቸው፣” ከሚሉት የተሳሳቱ ሰዎች ጋራ መስማማታቸው አይደለም ወይ? ኦሮሞዎች ለኢትዮጵያ ባዕዳን ከሆኑ ደግሞ ኦሮሞዎች የሚያነሱት የመብት፣ የነጻነት እና የመሬት የይገባኛል ጥያቄዎች ከቶውኑ እንዴት ሊሆኑ ነው? ነገሮች እየተስተዋሉ ቢሆኑ መልካመ ይመስለኛል:: የታሪካችን ሃቅ እደሚመሰክረው ግን ኦሮሞዎች ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠሩ የጠሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው::

በዚሁ ደብዳቤዎ ላይ ስለ ከምባታዎች፣ ሃዲያዎች፣ ወላኢታዎች እና ሌሎችም የደቡብ ሕዝቦች ደማቸውን ማፍሰስ እና አጥንታቸውን መከስከስ ጠቅሰው ነበር:: እነሱን ለምን እዚህ ላይ እንደጠቀሷቸው ግልጽ ባይሆንልኝም፣ እነሱ ምንም እንኳን የኦሮሞዎችና የዝርያዎቻቸውን ያህል ኢትዮጵያን ቢያንስ ለ 800 ዓመታት ገዝተው የማስተዳደር ዕድል ባይገጥማቸውም፣ ለአንዲት ደቂቃም እንኳን ኢትዮጵያዊነታቸውን ጥያቄ ውስጥ ያላስገቡና ሃገራቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነው ለመብታቸው የሚታገሉ ቆራጥ ኢትዮጵያውያን ናቸው::

የተወደዱ እና የተከበሩ ዶክተር በያን አሶባ ሆይ! ስማችንን እየሰነጣጠቅን ተራ ወግ ከምናወጋ ይልቅ እኔ ለርስዎ በጻፍኩት ግልጽ ደበዳቤ ውስጥ ሰለ አካተትኳቸው የኦሮሞውን፣ የአማራውን እና የሌሎቹን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን የወደፊት ዕጣ ፈንታ በሚጠቅሱት ቁም-ነገሮች ላይ ብንነጋገርና ለሕዝባችን የሚበጀውን መፍትሄ ብንመካከር በወደድኩ ነበር:: ሆኖም እርስዎ እንደአሉት አዲስ የተቋቋመው የእርስዎ የኦሮሞ ዲሞክራቲክ ግንባር ለኦሮሞውችና ለሌሎቹም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ የሚጠቅመውን መልካም ምላሽ እንደሚሰጥ ተስፋ አደርጋለሁ:: አያሌ ኢትዮጵያውያን መልሱን እየተጠባበቁ ነውና::

የሁሉም ነገር የመጀመርያ መፍትሄ፣ ስለአለፈው ግጭቶችና በደሎች ደጋግመው እያሰቡ ቂም ይዞ ከመራራቅ ይልቅ፣ ተቀራርቦ “ሰለ ፍቅር፣ በስመአብ ይቅር፣” ተባብሎ ታርቆ፣ ማንም ከማንም በላይ ያልሆነባትን፣ ሁሉም እኩል የሆነባትን የፍትህ፣ የነጻነትና የሰላም አገር አብሮ መገንባት ይመስለኛል:: ቀድሞ ተለያይተው ተራርቀው ይኖሩ የነበሩት አውሮፓውያን እንኳ የተባበሩትን አውሮፓ በኅብረት ፈጥረው በ ኢኮኖሚ እና በፖለቲካ ወደፊት እየገሰገሱ ነው:: እዚህ ላይ በብልሁና በአርቆ እስተዋዩ በኔልሰን ማንዴላ በ ደቡብ አሪካ የተከናወነውን ዕርቅ መዘከር ይገባል:: እንኳን እኛ በአንድ ምድር የተፈጠርን

ቀድሞውንም ምንጫችን አንድ ከመሆኑም በላይ እንደገና ተጋብተን ተዋልደን አንድ ደም እና አንድ አጥንት የሆንን፣ መልካችን እና ባሕላችን የተመሳሰለና የተዋሃደ ወንድማማቾችና እህትማማቾቹ ቀርተን፣ በግፈኞች ነጮች እስር ቤት ለዓመታት የቁም-ስቅላቸውን እየአዩ የማቀቁት ኔልሰን ማንዴላ፣ በጥቁርና በነጮች መሃል እርቅ ይውረድ ብለው፣ የይቅርታን መንፈስ አግዝፈው ደቡብ አፍሪካን ከቂም-በቀል የደም መፍሰስ እና ከመፈራረስ አድነዋታል።

የእኔን እና የእርስዎን ስሞች አስመልክቶ እርስዎ ከዚህ በላይ ለመነጋገር እንደ እማይፈልጉ ሁሉ፣ እርስዎ ሌላ መልስ እስከ አልሰጡኝ ድረስ እኔም በዚህ ዐይነቱ ፋይዳ-ቢስ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር አልፈቅድም። ስለ ሃገራችንና ሕዝባችን ጉዳይ ግን፣ ስሜተኛ ሳንሆን በታላላቅ ኦሮሞዎችና ኢትዮጵያውያን ጨዋነት፣ በሰከነ አእምሮ፣ ብሎም በቀና ልቦና እንወያይ ከአሉ ግን ግብዣዎን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ።

በመጨረሻም፤ እርስዎ እና ባልደረባዎችዎ ያሰባችሁት ቅዱስ ሃስብ እንዲሳካላችሁ ከልቤ እንደምተጋላችሁ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። እኔ ቀድሞውንም ያንን ግልጽ ደብዳቤ የጻፍኩላችሁ፣ ለሕዝባችን መፍትሄ የሚሆን የተቀደሰ አዲስ ሃሳብ ይዛችሁ ስለመጣችሁ "እሰየው! ደግ አደረጋችሁ!" ብዬ በቀና መንፈስ ነበር። አሁንም ቢሆን "በእምትችለው ሁሉ ተባበረን፣" ብላችሁ ከጋበዛችሁኝ ለዚህ የተቀደሰ አላማችሁ አብሬአችሁ ለመሰለፍ ዝግጁ ነኝ።

## ፍቅሬ ቶለሳ ጂግሳ (ዶ/ር)

***የእግርጌ መግለጫ***-- *ለ አዲሱ የኦሮሞ ዲሞክራቲክ ግንባር መፈጠር ድጋፍ ለመለገስና ለሕዝባችን ይጠቅማሉ ያልኳቸውን የ ግሌን ሃሳቦች ለመግለጽ፣ ባለፈው ጊዜ ለ ዶ/ር በያን አሶባ የጻፍኩት ግልጽ ደብዳቤ እኔ ባላሰብኩት ሁኔታ እንደ ቋያ እሳት ነድዶ፣ በኢትዮጵያ ሳይቀር አያሌ ውይይቶችን ከፍቷል። ይህን አስመልክቶ ብዙ መልካም አስተያየቶች ከበሰሉ ኦሮሞዎች፣ አማሮች፣ ትግሬዎች፣ ሃዲያዎች፣ ከምባቶች፣ ጋምቤላዎች፣ ሱማሌዎችና ሌሎችም በርካታ ኢትዮጵያውያን ከዓለም ዙሪያ ደርሰውኛል። የተቻለኝን ያህል መልስ ሰጥቻለሁ። አኔን በመስደብና ያለ ስሜ ስም በመስጠት ፍሬ-ቢስ ወይም እንቶፈንቶ ነገሮችን ጫጭረዋል። ለሁሉም መልስ ለመስጠት ጊዜና አቅም እንደሌለኝ በዚህ አጋጣሚ ልገልጽ እፈቅዳለሁ። እንደወንጀለኛ ስማቸውን ደብቀው ክብሪት ለሚጭሩት ደግሞ ምንም መልስ የለኝም። እኔ የማውቀውን እውነተኛውን የኦሮሞ እና የሌሎቹን ኢትዮጵያውያን ታሪክ በቀና መንፈስ ከልቡ ለመረዳት ለሚጓጓ ሁሉ ግን፣ አቅሜ በፈቀደ መጠን ታሪኩን ለማጋራት ምን ጊዜም ወደ ኋላ እንደማልል ለማረጋገጥ እወዳለሁ።*

*ከዚህ በተጨማሪ፣ ኦሮሞ እና አማራ ያልሆናችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ፣ የእናንተም የዘር አባታችሁ ኩሻዊው ኢዮጵ ነው። ከ ዛሬ 4000 ዐመታት በፊት እሱ እናታችንን እንቁዮጳን አግብቶ ዐስር ወንዶች እና ሶስት ሴቶች ልጆች ወልዶ ነበር። የወንዶች ልጆቹ ስም፣ "አቲባ፣ ቢኦር፣ ቢኦራ፣ ተምና፣ ኤቴር፣ አሻን፣ መሪሳ፣ ቴስቢ፣ ቶላ (የኔ አጎት ስም)፣ እና አዜብ" ናቸው። የሴቶቹ ደግሞ "ሱባ፣ ሚልካ እና ሎዛ" ናቸው። እነዚህም የታላቁ ኢትዮጵ ልጆች፣ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩትን እጅግ በርካታ ጎሳዎች፣ ነገዶች፣ ብሄሮች እና ብሐረሰቦች ሆነዋል። በእርግጥም አሁን የአሉት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ ከእነዚስ ሰዎች አብራክ የፈለቁ ናቸው። ስለዚህ ሁላችንም ቤተዘመዳሞች ነን። ለወደፊቱ፣ ዝርዝሩ እና ምንጩ ይፉ ይሆናሉ።።*

*ፍቅሬ ቶለሳ ጂግሳ (ዶ/ር)*

*እኤአ 06/01/2013*